## ምዕራፍ ፯

# ምጽዋት /ሥጦታ/

*«ከሚቀበል ይልቅ የሚሠጥ ብፁዕ ነው።»* (ሐዋ 20፥35) ጌታችን ለምን መስጠትን መረጠ?

❖ መስጠት የፍቅር መግለጫ ነው ።

ምጽዋት ያለህን ከሌላቸው ጋር የምትካፈልበት ፍቅራዊ ተግባር ነው። ፍቅር ያለው እግዚአብሔር አለውና ይህ ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር የሚወስድህ ሌላው መንገድ ነው። መስጠት፡- ያለህን ከእግዚአብሔር ጋር መካፈል ነው ብልህ ይደንቅህ ይሆን? ሊደንቅህ አይገባም። ለምን? ጌታችን ራሱ ስለተናገረው።

*«ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና. . .»* ከዚህ የሚቀጥለውን ወርቃማ ቃል ልብ በለው *«. . . እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት. . .»* (ማቴ 25፥35-40)

ስለዚህ አንተም ከሌላቸው ወንድሞችህ ጋር የተካፈልከው እያንዳንዱ ጥሪትህ ለአምላክህ እንዳደረግኸው ሆኖ መንገድ ይሆንሃል።

ወንድሜ፡- መስጠት እጅግ ጥንቃቄ ልታደርግበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለጽድቅ ያሰብከው መርገምን ሊያተርፍም ይችላል። ለምሳሌ ራበኝ ለሚልህ አንተ የማትበላውን ብትሰጠው፣ በረደኝ ለሚልህ የማትለብሰውን ብትሰጠው መስጠት ሳይሆን በማጣቱ ላይ መመጻደቅና የበላይነትህን ማሳየት ነው። ምጽዋት ወይም መንፈሳዊው ስጦታ ግን ያለህን ማካፈል -ማለትም ከምትበላው ማብላት፣ ከምትለብሰውም ማልበስ ነው።

*«እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው»* (ማቴ 7፥12)

ምጽዋት በዚህ ብቻ የተሰወነ ሳይሆን በሀሳብ ለተቸገረ፣ ማህበረሰቡ ላገለለው፣ በሽታ ላጠቃው ለመሳሰለው ሁሉ ፍቅር መስጠት / ማካፈል ነው።





ለተጨነቀ፣ መፍትሔ ሳጣ፣ መላ መጠቆም መውጫ ማሳየት ሁሉ ያለህን ማካፈል ነው ።

ምጽዋት ያለህን ብቻ ሳይሆን አንተነትህን ለሌሎች መስጠት ነው። ለራሱ ብቻ በመኖር ከክርስትና ጀርባ የቆመ ሰው መቀበልን እንጂ መስጠትን አያውቅም። ራሱን ያገለለው ደግሞ አይቀበልም አይሰጥም። ማህበራዊ ሕይወትን በግርድፉ የሚኖረውም የሚቀበል -የሚሰጥ ነው። ክርስቲያን ግን መቀበሉን ሳያስብ የሚሰጥ ነው። ቢሰጥም ከራሱ የተቀበለውን ነው። ወይም ነገ የሚጠብቀው ምላሽ ሳይኖር ነው። ምክንያቱም እውነተኛው ክርስትና «እኔ» ሳይሆን «እኛ» እያሉ የሚኖሩት ሕይወት ነው። ይህ ዓይነቱ ሥነ ምግባር ደግሞ ራስን የመካድ ደረጃ ላይ ለደረሱ የሚቻል ስለሆነ በጀመርከው ጉዞ ቀጥልበት። «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» (ማር 8፥ 34) ክርስቶስን የተከተለ ሰው ግላዊነት ያጠቃው ሊሆን አይችልም። ወንድሞቼ፣ ወገኖቼ ማለት የቻለ ብቻ እውነተኛ ክርስቲያን ነው።

እጅግ ረሀብ በጸናበት ዘመን ላይ ሆና፣ ካላት ትንሽ ነገር ላይ አካፍላ ለኤልያስ የሰጠችውን፣ እግዚአብሔርም ቤቷን በበረከት የሞላላትን የስራፕታዋን መበለት ተግባር አስተውል። (1ነገ17፥11-19) የሰጠችው የተረፋትን ወይንም የማትፈልገውን አይደለም። ልጇና እሷ በልተዋት ለሞት ከተዘጋጁባት ጥቂት ዱቄት ከፍላ እንጎቻ አድርጋ ሰጠችው። መካፈልና እኛ ማለትን የሚያውቁትን የእግዚአብሔር በረከት ይጎበኛቸዋል

ጌታችን ከሁሉ የሚበልጥ ስጦታ እንደሰጠች የመሠከረላት መበለትስ ምን ዓይነት ስጦታ አቅርባ ነው? (ሉቃ 21፥1-4)

«ዐይኑንም አንስቶ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለጠጎችን አየ አንዲትም ድሃ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል አየና ፡- እውነት እላችኋለሁ፣ ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች። እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና። ይሕች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ።»

እንግዲህ መስጠት ከማግኘት ከማትረፍ አይደለም ማለት ነው። ከዚህች መበለት በቁጥር በመጠን አብልጠው የሰጡ አሉ። ያላትን በመስጠት ግን ይህች መበለት በለጠቻቸው ። ምክንያቱም እነርሱ ከትርፋቸው ሰጥተዋልና። የዚህች መበለት ተግባር ከላይ የሰፈረውን ሁሉ በጉልህ አጉጸባርቆ የሚያሳይ ነው» ለራስ

ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መኖርን የሚያስተምር ነው። ደግሜ እልሃለሁ «ክርስትናም ፍቅር ነው። እንደ ቅዱስ አባት ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እንደነቅዱስ ባስልዮስ የድሆች ቁስል ከተሰማህ ረሀባቸው ከራበህ አንተ ክርስቲያን ነህ ። እስከ መስዋዕትነት ለመድረስ ከችግረኞች ጎን ከቆምክ፣ የሚያስፈልግህ ሁሉ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ካመንክ እውነትም የክርስቶስ ተከታይ ነህ።

❖ እግዚአብሔር የሥጦታህን ብዛት ሳይሆን ምንጬን እንደሚመለከት ተማርክ? ለጋስነትን ለማሳየት ከሚደረግ ዕልፍ ምጽዋት በፍቅር የሆነች አንድ ሳንቲም ልዩ ሥፍራ አላት። የምትሰጠውንም ሰው ስጦታህንም እየወደድክ አድርገው። ከአንተ እንዲወጣ ብቻ ወይም እንደግዴታ ቆጥረኸው ብትሠጥ ወደ እግዚአብሔር አይወስድህም። ደስ እያለህ ለመንፈስህ እርካታ የሚሆን ስጦታን ስጥ።

❖ በደስታ የሚሰጥን እግዚአብሔር ይወደዋል።

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጥን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ። በኃዘን ወይም በግድ አይደለም።» (2ቆሮ 9፣7)

ችግረኛን ለመርዳት ስትነሳ በፍቅር ተገፍተህ ተነሳ። ራሱ ችግረኛው ሰው ከምትሰጠው ስጦታ ይልቅ ያሳየኸው ፍቅር ደስ ያሰኘዋል። ፍቅር አልባ ስጦታ ብትሰጠው ግን የጠቀምከው እየመሰለህ ስሜቱን ታቆስለዋለህ። ስላለህ ወይም ከማግኘት ተነስተህ የምትሰጠው ቢሆን ታናሽነቱን በሌላ ቋንቋ እየነገርክ ትጎዳዋለህ። ስለዚህ በልጁ ደስታ ለመደሰት የአቅሙን ሁሉ እንደሚያደርግ ደግ አባት በፍቅር ደስ እያለህ ስጥ። ለወንድምህ ያደረግኸው ለእግዚአብሔር እንዳደረግኸው ይሆንልሃልና። በዳዊት ዘመን የእግዘአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ሕዝቡ ሁሉ ያላቸውን ሲሰጡ የነበራቸውን ደስታ መጽሐፍ ቅዱስ ያስነብብሃል።

«ሕዝቡም ፈቅደው ሰጥተዋልና፣ በፍፁም ልባቸውም ለእግዚአብሔር በፈቃዳቸው አቅርበዋልና ደስ አላቸው። ንጉሡም ዳዊት ደግሞ ታላቅ ደስታ ደስ አለው ።» (1ዜና 29፣9-16)

ዳዊት ከደስታው ብዛት ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋገረበት ይህ ቃል ደግሞ እጅግ ታላቅ ትምህርትን የሚሰጥ ነው።





*«ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና ፣ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ ?ሕዝቤስ ማን ነው?. . .አቤቱ አምላካችን ሆይ ለቅዱስ ስምህ ቤት እንሰራ ዘንድ ይህ ያዘጋጀነው ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው ሁሉ የአንተ ነው። አምላኬ ሆይ ልብን እንድትመረምር ቅንነትንም እንድትወድ አውቃለሁ። እኔም በልቤ ቅንነትና በፈቃዴ ይህን ሁሉ አቅርቤአለሁ። አሁንም በዚህ ያለው ሕዝብ በፈቃዱ እንዳቀረበልህ አይቻለሁ. . .»*

እባክህ ይህን የተወደደ ቃል ጨርሰህ ፣ ደጋግመህ አንብበው። ወንድሜ ዛሬም ከአጠገብህ እየፈረሰ ያለው የእግዚአብሔር ቤት የሰው ልጅ ነው ። (1ቆሮ 3፣16) እናም በፈቃድህ ደስ እያለህ፣ እግዚአብሔር የሰጠህን ስጠው ። ከሌለህ ፍቅርህን መግበው። ለመሆኑ ይህን እጅግ ውብ የሆነ ቃል አስተውለኸዋል ? «ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና. . . .»

ልብ በል! የራስህ የሆነ አንድም ነገር የለም። አንተ የእግዚአብሔር ነህ። ያለህም ከእርሱ የተሰጠህ ነው። (ኢሳ 43:1) የኢዮብንም ቃል በልብህ መዝገብ አኑረው። «ራቁቴን ከእናቴ ማህፀን ወጥቻለሁ። ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሳ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» (ኢዮ 1፣21)።

ስለዚህ አንተም እንደነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች እያሰብክ የምትሰጠው የተቀበልከው መሆኑን ዐውቀህ ስጥ።

❖ ግን እግዚአብሔር፡- ድንቅ መካር ኃያል ሲሆን ከእኛ ከደካሞቹ ሊቀበል መፍቀዱ አይገርምህም?። አቤት ትሕትና ! ዳዊት ይህ ነገር ቢያስገርመው «እኔ ማን ነኝ» ማለቱን አይተሃል። እግዚአብሔር ሀሳባችንን እንድንገልጽ ዕድል ሠጠን። ልክ ከሕፃን ልጁ ስጦታን እንደሚቀበል አባት አስበው ። ልጁ እያደረገ ያለው የፍቅር ስሜቱን መግለጽ ነው። ስጦታው ግን አባቱ ከሠጠው -የተቀበለው ነው ። ዳዊትም «ከእጅህ የተቀበልነውን ሠጠንህ» ያለው እንደዚሁ ነው ።

እግዚአብሔር መስጠትን የሚያስተምርህ እየሰጠ ነው። ሕይወትን ሰጠህ፣ የሕልውናህም ዋስትና እርሱ ነው። ሕይወትህን አለአግባብ ብትመራው አሁንም በፍቅሩ ዋጀህ። ዛሬ አንተ ያለህን ብትሰጥ ሕይወትህን ሰጠህ ይባላል።

ነገር ግን ሕይወትህም ከእርሱ የተቀበልከው ነው ። ስለዚህ አምላክህን «ጤናና ጉልበት ስጠኝ፣ እኔም የሰጠኸኝን በመስጠት አገለግላለሁ።» እያልክ ለምነው።

«አምላኬ ሆይ አንተን ለማገልገል ብነሳ ለአንተ የምጨምርልህ አንዳች ነገር እንደሌለ አምናለሁ። ምክንያቱም ጤናውም ጉልበቱም ዕውቀቱም ያንተው ናቸው ። ከመነሻው ለአገልግሎትህ ያደረብኝ ፍቅር ከአንተው ነው። እኔም ራሴ ያንተው ነኝ። በሰጠኸኝ ሕይወት አንተን አገለግላለሁ። ለድሆች፣ ለችግረኞች መጽናኛ እሆን ዘንድ አሁንም ቃልህን ስጠኝ። የሠጠኸኝንም እንድሰጥ እርዳኝ።» በለው

<u>እንዴት መስጠት አለብህ</u> ?

❖ ክብርን ለመፈለግ አትስጥ

በአንደበትህም ይሁን በልብህ ፣ በስሜትህም ይሁን በሀሳብህ የራስህ ነገር ኖሮህ እንደሰጠህ አስበህ አትኩራራ። ለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን እንደትልቅ ማስረጃ ተጠቀም። *«አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልክ ከሆነ ግን እንዳልተቀበልክ የምትመካ ስለምንድር ነው?»* (1 ቆሮ 4፣7)

ስለዚህ ስጦታ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተቀብለን የምንሠጠው እንጂ የራሳችን እንደሆነ በከንቱ የምንመካበት አይደለም ።

❖ ስጦታህ (ምጽዋትህ) በምስጢር ይሁን ።

*«አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን፣ ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ ። በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል ።»* (ማቴ 6፣4)

እግዚአብሔር ያለህ ምጽዋትህ ከሰዎች እንዲሰወር ብቻ ሳይሆን ከአንተም ከራስህ ጭምር ነው። ይህን ያህል ሰጠሁ ፣ ይህን አደረግሁ እያልክ እንዳትቆጥርም ነው ። የምትችለውን ሁሉ እያደረግህ ምንም እንዳላደረግህና ብዙ እንደሚቀርህ ካልተሰማህ ዲያብሎስ እየፈተነህ ነው ። ይልቁንም ዋጋህ ሁሉ በምድር እንዳይቀርብህ ጥንቃቄ አድርግ።

❖ በልግስና ስጥ

«የሚሠጥ በልግሥና ይስጥ» ሮሜ 12፣8። ይህ ቀደም ሲል እንደ ግዴታ ቆጥረህ መስጠት እንደሌለብህ የተነጋገርነውን ለማጽናት ቅዱስ ጳውሎስ የሚናገረው ነው። *«እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው*





*መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፣ መልካምን እንዲያደርጉ ፣በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ ፣ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው፣፣»* እያለ የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስን ሲያበረታታም ታገኘዋለህና አንተም ይህን በመሰለው ሁሉ በርታ። (1ጢሞ 6፣18)

*«በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል ፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል።»* (2ቆሮ 9፣6) ። እነዚህን ቃላት ጌታችንም ለአንተ በሚገባህ መልኩ እንዲህ ሲል አስቀምጦልሃል። *«ስጡ ይሰጣችሁማል፣ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና . . .»* (ሉቃ 6፣38)

እንግዲህ ስጦታን (ምፅዋትን) መስጠት ብቻ ሳይሆን ቸር መሆን ይጠበቅብሃል። ምሳሌ ይሆንህ ዘንድ የዳዊትና የኦርናን ውይይት አስተውል። ዳዊት ለእግዚአብሔር መሠዊያን ይሰራ ዘንድ ከኦርና አውድማውን ለመግዛት ፈለገና ጠየቀው ። *«መቅሠፍቱ ከሕዝቡ ላይ ይከለከል ዘንድ አውድማውን ከአንተ ገዝቼ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ልሠራ ነው»* አለው ። ኦርናም ዳዊትን ጌታዬ ንጉሡ እንደወደደ ወስዶ ያቅርብ ፣ እነሆ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች፣ ለሚቃጠል እንጨት የአውድማ ዕቃና የበሬ ቀንበር አለ። ይህን ሁሉ ኦርና ለንጉሡ ይሰጣል አለው። ኦርናም ንጉሡን፡- አምላክህ እግዚአብሔር ይቀበልህ አለው፡፡- - -» (2ሳሙ 24፣22)። ዳዊት ኦርናን የጠየቀው በሽያጭ ሲሆን ኦርና ግን በልግስና ሊሰጠው ወደደ። ምክንያቱም ይህን ሁሉ ከእግዚአብሔር የባሕርይ ልግስና የተቀበለው እንደሆነ ያምናልና። ነገር ግን ዳዊት ያለዋጋ መሥዋዕት ሊያቀርብ ስላልወደደ እንዲሸጥ ግድ አለው (2 ሳሙ 24፣ 24-25) ነገር ግን ሁለቱም ያላቸውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ደስተኞች ለጋሶችና ቸሮች ነበሩ።

ከዚሁ ጋር የአብርሃምንም ደግነት፣ እንግዳ ተቀባይነት አስታውስ። (ዘፍ 18፣6-8) ለአብርሃም መካፈል የደስታ ምንጬ ነበር። የደከመን ስለሚያሳርፍ የተራበን ስለሚያበላ፣ ሁሉን በእኩልነት ስለሚቀበል የዘለዓለም አምላክ ሥላሴ በቤቱ ተስተናገዱለት። እርሱ ለማንም ሊሰጠው የማይችለውን ታላቅ ስጦታ ልጁን ይስሐቅን ከሥላሴ ተቀበለ። ነገር ግን ልጁንም ቢሆን ለእግዚአብሔር ለመስጠት አላመነታም። ከእርሱ የተቀበለው ነውና። «አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ። . . .»(ዘፍ 22፣1-19)

ወንድሜ አንተም ለተቸገሩ ቸርና ለጋስ ሆነህ እግዚአብሔር አብልጦ እንደማይሰጥህ መርምር (ሚል 3፣10)። ባለህ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ኑር። «እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር ከፍሬህም ሁሉ በኩራት፣ ጎተራህም እህል ይሞላል። መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።» (ምሳ 3፣9)

❖ ያለህን መስጠት፣ በሙሉ ልብህ ክርስቶስን መከተል የምትችልበት ምስጢር ነው ።

«ፍፁም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ።» (ማቴ 19፣21)። ሌላም ጌታችን ያለህ አለ። «ያላችሁን ሽጡ፣ ምጽዋትም ስጡ። ሌባ በማይቀርብበት፣ ብልም በማያጠፋበት በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ። መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናል።» (ሉቃ 12፣33)

❖ <u>ምጽዋትህን ፍፁም ለማድረግ</u>፦ በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ እንዲመለስልህ የምትጠብቀው ነገር አይኑር። ለመስጠት ስታስብም መጠየቅን አትጠብቅ። ብቻ የአንተ የሆነው የወንድምህ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር እንደሆነ እያሰብክ ለሚያስፈልጋቸው፣ የተቻለህን አድርግ። (ሉቃ 3፣11)

እግዚአብሔር ለእኛ ሳንለምነው የምንሻውን ዐውቆ የሚሰጠን አምላክ ነው። እናት የልጇን ፍላጎት ዐውቃ አስቀድማ እንደምታደርግለት ያለ ነው። አምላክህ ከአንተም የሚጠብቀው ይህንን ነው። በፍቅር የሠጠህን በፍቅር ስጥ። አንተም ለወንድም እህቶችህ እንደዚሁ አድርግ።

❖ ለመስጠት ቀጠሮ አያስፈልግህም ፣ ወይም አትዘግይ። ምናልባትም ባንተ መዘግየት ለአደጋ የሚጋለጥ ሕይወት ይኖራልና ። ጥበበኛው ሰሎሞን ይህን በተመለከተ የተናገረውን ስማ። «ለተቸገረው ሠው በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል፣ ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን፣ ወዳጅህን ፦ ሂድና ተመለስ፣ነገ እሰጥሃለሁ አትበለው ።» (ምሳ 3፣27)

<u>ምጽዋት ብዛት ወይስ ጥራት ?</u>

❖ የማትፈልገውን ሳይሆን ለአንተ ምርጥ የምትለውን መስጠት ልመድ። የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ ልብስ፣ ለመመገብ አስቸጋሪ የሆነ፣ የሻገተ ወይንም የደረቀ ምግብ መስጠት የተለመደ በሆነበት ዘመን ላይ ስላለህ የምታደርገውን





ሁሉ ተጠንቅቀህ አድርግ። አንተ የማትለብሰው ስለማይለበስልህ ነው። የማትበላው በጤናህ ላይ ችግር ስለሚያስከትልብህ ነው። ታዲያ ወንድምህስ? የምትሰጠው ለሕመም የሚዳርገውን ነው? መሆን የለበትም። ይልቁንም ለወንድምህ ከምትበላው አካፍለው። ከምትለብሳቸው ሁለቱ ልብሶች አንዱን ስጠው ። የሚጎዳውን ብዙ ነገር ከምትሠጠው የሚጠቅም ትንሽ ነገር ስጠው። ለአንተ የምትመኘውን ጥራት ለወንድምህም አድርግ። «ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው» ያለውን የእግዚአብሔር ቃል መለስ ብለህ አስብና፣ የምትሰጠውን ጎጂ ነገር ለክርስቶስ እንደምትሰጠው ተረ።

ከዚሁ ጋር አቤልና ቃየል ለእግዚአብሔር ያቀረቡት መሥዋዕት እንዴት እንደነበረ አስብ። «አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኩራትን ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ።» (ዘፍ 4፣4) ለምን መረጠለት? ብትል፣ ካለው ሁሉ መርጦ የተሻለውን ስላቀረበ ነው። በሐዋርያት ሥራ 4፣34-35 ላይ ሠፍሮ የሚገኘውን የሐዋርያቱ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበረ የሚናገረውን ቃል አስተውለህ አንብበውና የአንተ ምጽዋት የአንተ ሥጦታ የትኛው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ራስህን ጠይቅ።

<u>የእግዚአብሔር ድርሻ</u>

እግዚአብሔር ያለህን የሚካፈልህ ሊጠቀምበት ሳይሆን ሊባርክልህ ነው። ለአንተ የማግኘትህ፣ የሀብትህም ምንጭ እርሱ ነው። ከበጎ ተግባር ሁሉ ተካፋይ ትሆንለት ዘንድ ይካፈልሃል። ስትሠጠው ልትጠቅመው ሳይሆን እውነተኛ ሥጦታን፣ ፍቅርን ሊያስተምርህ ነው። ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው ጌታ በአንተ አቅም የምትሠራው ትንሿ ነገር ታስደስተዋለች። ለእግዚአብሔር በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሳያጣ የሚቀበልህን የእግዚአብሔርን ትሕትና ትማራለህ። እርሱ ትሑት ስለሆነም አንተም ትሑት ትሆናለህ (ማቴ 11፣29)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸውን ስጦታና ሀብት በአሥራት በበኩራት መልክ ድርሻው አድርጎ ይቀበላቸው እንደነበረ እናስታውሳለን። እነዚህ ከየት አምጥተው መሥዋዕት አቀረቡ? እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነው። በቅንነት በፍቅር ያደረጉትን ወድዶ ተቀብሏቸዋል። ዛሬም በክርስትና ውስጥ አድጎ የምታገኘው ይህንኑ ነው። ክርስቶስ ራሱን ሰጥቶ መስጠትን አስተምሮሃል ። ለሰው ሕይወቱን ከመስጠት ሌላ ምን ነገር ይኖረዋል

? ሁሉን ያደረገው ሁሉን መስጠት ያስተማረው ጌታ ድርሻው አድርጎ የጠየቀህ ግን እጅግ በጣም ቀላሉን ነው ። ቀጣዩን ነጥብ ተመልከት ።

## <u>አሥራት</u>

ሕግ ከመፃፉ በፊት ሕግ ከመጻፉም በኋላ ትውፊትን መሠረት አድርጎ ሲተላለፍልን የቆየ እግዚአብሔርን የመታዘዣው መንገድ አሥራት ነው። ስለ አሥራት ከአባታችን ያዕቆብ የሰማነው ምንድን ነው?

ያዕቆብ ባደረበት ሥፍራ ላይ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደሰማይ ደርሶ የእግዚአብሔርም መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ተመለከተና እንዲህ አለ። «. . .እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፣ በምሄድባትም በዚህች መንገድ ቢጠብቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፣ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል። ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል። ከሠጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጣለሁ።» (ዘፍ 28፣1-22) ያዕቆብ አሥራትን አባቱ ለመልከጼዴቅ እንዳቀረበ በትውፊት ተላልፎለት አግኝቶ ነው። (ዘፍ 14፣20) «አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው »

- በእግዚአብሔር የታዘዘ ነው።

ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን ይመራ በነበረበት ዘመን ላይ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ። *«ከእርሻህ በየዓመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ»* ( ዘዳ 14፣22)

«የምድርም አሥራት፣ ወይም የምድር ዘር ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው። ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው።» (ዘሌ 27፣30) *«የእህልህን፣ የወይን ጠጅህን፣ የዘይትህንም አሥራት፣ የላምህንና የበግህንም በኩራት፣ የተሳልኸውንም ስእለት ሁሉ፣በፈቃድህም ያቀረብከውን በእጅህም ያነሳኸውን ቁርባን በደጆችህ ውስጥ መብላት አትችልም።»* ( ዘዳ 12፣17/ ዘዳ 14፣23)

በአጠቃላይ ይህንን ሁሉ ቀራጩ እንዲህ ሲል በአጭሩ አስቀምጦታል። «ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ።» (ሉቃ 18፣12)
ያዕቆብንም መላልሰህ አስበው *«ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንዱን እሠጣለሁ ።»* (ዘፍ 28 ፣22)

- አሥራት የማይሠጥ እግዚአብሔርን እንደሰረቀ ይቆጠራል ።





«ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃል ? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም የሰረቅንህ በምንድር ነው ? ብላችኋል። በአሥራትና በበኩራት ነው» (ሚልክ 3፣8-10)

### <u>ለእግዚአብሔር የማይሰጥ</u>

ሁሉን በፍቅር ለሚሰጥ ለእግዚአብሔር የማይሰጥ ነገር ቢኖር የአመፃ ገንዘብ ብቻ ነው። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ፣ በቅሚያ፣ ድሃን በመበደል፣ ከሕጋዊ ባለቤቱ በመንጠቅ የመጣ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ይጸየፈዋል። እግዚአብሔር በባሕርዩ ንጹሕ ነውና ንጹሕ ነገር ይወዳል። በወንጌል ያስተማረንም ይህንን ነው።

*«የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘለዓለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ»* (ሉቃ 16፣9)

አሥራት የምትሠጠው ብዙ ስላለህ ብቻ እንደሆነ አታስብ። ያላትን ሁሉ የሠጠችውን መበለትም አትርሳት (ሉቃ 21፣4)

### <u>የስጦታህ ትንሹ አሥራት ነው ።</u>

አሥራት በመሠረቱ ከእሥራኤላውያን ወይም ከብሉይ ኪዳን የመጣልን ነው። ለእኛ ለክርስቲያኖች ግን ከዚህም በላይ የሚጠበቅብን አለ። *«ለሚለምንህ ስጥ»* (ማቴ 5፣41)
*«ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ። . . . ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ።»* (ማቴ 6፣19) ስለዚህ አንተም አሥራትን በማውጣት አትገደብ ። የተቸገሩትን እርዳ። የተራቡትን አብላ። የታረዙትን አልብስ ። በአጠቃላይ በበጎ ሥራ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሁን ። አሥራትን አውጥቻለሁና የሚገባኝን ፈጽምኩ ብለህ አታስብ። እንደዚህ ካሰብክ ለችግረኛው ጩኸት ጆሮህ የተዘጋ ይሆናል። አንተ ሰሚ ካልሆንክ ደግሞ እግዚአብሔርም አይሰማህም። *«የድሃውን ጩኸት እንዳይሠማ ጆሮውን የሚደፍን ሠው ፣ እርሱ ራሱ ይጮኻል፣ አይሰማለትምም»* (ምሳ 21፣13) ፍቅርህ በልብህ ፍጹም ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ሂሳብ አትስራ ። በጎ ሥራ የመሥራትን ዕድል ባገኘህበት አጋጣሚ ሁሉ ልብህ ክፍት ይሁን ።

- ምጽዋትህ ከቀራጩ የበለጠ ይሁን ።

ክብር ምሥጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችንም የተናገረህ ይህንኑ ነው። *«ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ ወደመንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም»* (ማቴ 5፤20) ። ጻፎችና ፈሪሳውያን አሥራት ያወጡ ምጽዋት ይሰጡ እንደነበረ ምንም ጥርጥር የለውም። ህግን በቃል ብቻ የምትተረጉም እንዳትሆን በምፅዋትህ፣ በፍቅር ስጦታህ ከእነርሱ የምትበልጥ ሁን። ፍጹምነትን ስትሻ ሁሌም ከድሆች እንደሚያገናኝህ አትዘንጋ (ማቴ 19፤21)

አሥራት በንብረትህ ውስጥ ብቸኛው የእግዚአብሔር ድርሻ አይደለም። ስለዚህ ስለሌላኛውም እንነጋረር ።

<u>በኩራት</u>

በኩራት ማለት እግዚአብሔር ከሰጠህ ሁሉ ላይ የመጀመሪያውን ለእርሱ መስጠት ማለት ነው ። አቤልም ያደረገው ይህንኑ ነበር። (ዘፍ 4፤4) የሚገርምህ ደግሞ የተጻፈለት ሕግ ሳይኖር ነው ይህን ያደረገው ። ምርጡን መረጠ፣ የመጀመሪያውን ለየ ፤ ለእግዚአብሔርም ሠጠ። ስለዚህ እግዚአብሔር በአቤል ፍቅር ደስ አለው። አሁን ግን ለእኛ የተጻፈልን የበኩራት ሕግ አለ ።

«በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማህፀንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው።» (ዘጸ 13፤2) ። ከሰው በኩር የሆነ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል ይለይ ነበር። ኋላ በአሮንና በሌዊ ቤተሰብ ከመተካቱ በፊት ማለት ነው። ከእንስሳም በኩር የሆነው የእግዚአብሔር ነበረ፣ ነውም።

❖ በኩራት ከአሥራት የበለጠ ሥጦታ ነው።

ምክንያቱም አሥራት ካለህ ሁሉ ከአሥር አንድ እጅ መስጠት ማለት ነው ። (100 ብር ቢኖርህ 10 መስጠት እንደማለት)። በኩራት ግን በመጀመሪያ ያገኘ ኸውን ያለህን ብቸኛ ነገር መስጠት ማለት ነው ።

ለምሳሌ ሐና አንድ ብቸኛ ልጅ ሳሙኤልን ወለደች ፤ እሱኑ ለእግዚአብሔር ሠጠች። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ዮሐንስን ብቻ በብዙ ስለት ወለዱ እሱኑ ሰጡ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእመቤታችን አንድና ተከታይ የሌለው ልጇ ሲሆን እሱም ለራሱ ለመስዋዕትነት ቀረበ። የጌታችን በኩርነት ግን ተከትሎት የሚወለድ ኖሮ ሳይሆን፣ ለእናቱ በዘመን ሁሉ አንድ ልጇ ነው። በዕብራውያን /በእሥራኤላውያን ባህል ደግሞ ለበኩር ልጅ የሚሠጠው ደረጃ ፍቅርና ክብር ልዩ ነው። እና እነዚህን ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት እግዚአብሔርን ከሁሉ ነገር በላይ ማስቀደም፣ ማክበር ማለት ነው። ስጦታውም ከሥጦታዎች ሁሉ





የሚበልጥ ሥጦታ ነው። የበኩራት ሕግ በበኩር ልጅ ስጦታ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የምድርን ዘር ፍሬ ከእፅዋት ከአትክልት የሚገኘውን ሁሉ የሚጨምር ነው። *«የተመረጠውን የምድርህን ፍሬ በኩራት ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጣ»* (ዘጸ 23፤19)

*«ወደ ምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ፣ መከሩንም ባጨዳችሁ ጊዜ የእናንተን መከር በኩራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ። እርሱም ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠምርላችሁ ይወዝውዘው»* (ዘሌ 23፤10) ፤ዘዳ 26፤2-10።

❖ የእንስሳንም በኩር ለመስጠት ታዟል ።

*«ማሕጸንን የሚከፍተውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለይ፣ ከሚሆንልህ ከብት ሁሉ ተባት ሆኖ አስቀድሞ የተወለደው ለእግዚአብሔር ይሆናል።»* (ዘዳ 13፤12)፣ (ዘዳ 34 ፤19)

የመጀመሪያህን (በኩርን) ለእግዚአብሔር ሰጠህ ማለት እግዚአብሔርን የመጀመሪያህ አደረግህ ማለት ነው። ስለዚህም ያለህ ሁሉ በእግዚአብሔር የተባረከ ይሆናል።

❖ በዚህ ባለንበት ዘመን ላይ የበኩራትን ሕግ እንዴት መፈጸም ይቻላል? ሕዝቡ ሁሉ በግብርና የሚተዳደርና የምድርን ፍሬ የሚሰበስብ አይደለም። ሁሉም ከብትና በግ አርቢ ነው ማለትም አይቻልም።

## ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን?

ለምሳሌ ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆንክ ከደመወዝህ የመጀመሪያውን እንደ በኩራት ለእግዚአብሔር መስጠት ትችላለህ። ነጋዴ ብትሆን የመጀመሪያ ትርፍህን መስጠት ትችላለህ። የመጀመሪያ የደመወዝ ጭማሪህን፣ የመጀመሪያ የትርፍ ሰዓት ክፍያህን፣ የመጀመሪያ የማካሻ ክፍያህን ለእግዚአብሔር ከሰጠህ የበኩራትን ሕግ ፈጸምክ ማለት ነው።

<u>ስእለት</u>

ስእለት ከአሥራትና ከበኩራት በዓይነቱም በአፈጻጸሙም የተለየ ሥጦታ ነው ። ይህ አንተ ለእግዚአብሔር የገባኸውን ቃል የምትፈጽምበት ነው። በጭንቅ በመከራ ውስጥ ሆነህ ችግሮች እንዲቀሉልህ፣ እንዲያልፉልህ ለእግዚአብሔር ትሳላለህ። ተፈጽሞልህ ስታገኝ የገባኸውን ቃል ማለትም እሰጣለሁ ያልከውን ትሰጣለህ። ስእለት ማለት ይህ ነው።

የተሳልከውን ሳታዘገይና ሳትለውጥ ስጥ:: *«ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ የተሳልከውን ፈጽመው:: ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል»* (መክብብ 5፥4-5)

ስእለት የገንዘብም የእውቀትም የሕይወትም መሆን ይችላል:: ልትፈጽመው የማትችለውን ግን በፍጹም አትሳል:: ከዚህ ይልቅ ፍላጎትህን ለእግዚአብሔር ገልጸህ በመንገር እንዲፈጽምልህ መለመን ይመረጣል:: «ጌታዬ ሆይ እኔ ይህን አስባለሁ:: መፈፀም መቻሌን ግን እጠራጠራለሁ:: እኔ ደካማ ነኝና የሀሳቤን የማደርግበት ኃይልን አንተ ስጠኝ - - -» ብለህ ጠይቀው::

ቁርባን /መባ/

ቤተ ክርስቲያን መባን ለሚያገቡ ሰዎች ሁሌም ጸሎት ማድረግዋን አታቋርጥም:: ከዚህ ቋሚ ጸሎት አንተም ድርሻ ሊኖርህ ይገባል::

«ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንለምናለን:: ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባ ስለሚያገቡ፣ መሥዋዕቱን፣ ቀዳምያቱን ከአሥር አንዱን የመታሰቢያ ምሥጋና ብዙውና ጥቂቱን የተሰወረውና የተገለጸውን ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ3 . . .»

አቅምህ በፈቀደ መጠን አምላክህ ይመሠገንበት ዘንድ መብራቱን፣ዕጣኑን፣ ዘይቱን እንድትሰጥ የትሕትና አምላክ ፈቅዶልሃል:: ይህን ባትችልና ባታደርግ ደግሞ ፈቃድህን ይቀበልሃል:: በአጠቃላይ በአንተ ምክንያት እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሁኔታ ተመቻችቶልሃል:: አሁን ከአንተ የሚጠበቀው በተሰጠህ እድል መጠቀም ነው::

ወንድሜ በስጦታህ በርታ:: መልካም ፈቃድህንም አሳድግ:: ቅንነት፣ ሰላማዊነት ፣ ፍቅር የክርስቲያናዊ ሕይወትህ መገለጫዎች ይሁኑልህ:: ከተሰጠህ ላይ ከፍለህ በመስጠት ኑሮህን ከእግዚአብሔር ጋር አድርግ:: በበጎ ምግባር እየኖርክ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስህን መንገድ አቅና:: ጉዞህን ለሚያደናቅፍ ሌላ ስሜት ሁሉ ዕድል አትስጥ::

የተሰጠህን በመስጠት አምላክህን ደስ እንድታሰኝ እግዚአብሔር ይርዳህ::

*«በፊቴም ባዶ እጃችሁን አትታዩ»* (ዘጻ 13፥25) ዘጻ 34፥20